# የዲስትሪክቱ ኗሪ ነኝ፥ ሁለቱም ሜዲኬርም ሜዲኬድም አለኝ። የቱ የቱ ነው? የትኛው ነው ምን የሚያደርገው?

<u>**ሜዲኬር**</u> ብቁነት ላላቸው ሰዎች በዋናነት ዕድሜያቸው ከ65 ዓመት በላይ ለሆኑ ወይም የአካል/የአእምሮ ጉዳት ላላቸው ሰዎች የሕክምና ሽፋን የሚያቀርብ ፌዴራል መርሃ ግብር ነው። ሜዲኬር በመደበኛም ሆነ በሕመም ምክንያት የሚደረግ ሕክምናን ይሸፍናል፥ ለምሳሌ ዶክተር ጋር መሄድና በሆስፒታል መተኛትን ጨምሮ።

በዲስትሪክቱ ውስጥ ሜዲኬር ሽፋን ሊሰጥዎ የሚችልባቸው ጥቂት የተለያዩ መንገዶች አሉ።

ብዙ ሰዎች አልፎ አልፎ “original Medicare” (“የመጀመሪያው ሜዲኬር”) ተብሎ የሚጠራው “fee-for-service” (“ክፍያ ለአገልግሎት”) አላቸው። ይህ ሽፋን ካልዎት ምናልባት ከላዩ “Medicare Health Insurance” (“ሜዲኬር የጤና ዋስትና”) የሚል ቀይ፥ ነጭና ሰማያዊ ካርድ ሊኖርዎት ይችላል። ይህ ሽፋን ለተመላላሽ ሕክምናም በሆስፒታል ለማደርም ይከፍላል።




ሌሎች ሰዎች የሜዲኬር ጥቅማጥቅሞቻቸውን የሚያገኙት በግል የጤና ዋስትና በኩል ነው። ይህም Kaiser Permanente (ካይዘር ፐርማኔንቴ)፥ Aetna (ኤትና) ወይም ሌላ ኩባንያ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ዋስትናዎች በሜዲኬር fee-for-service ከሚያገኟቸው ጥቅማጥቅሞች ጋር አንድ ዓይነት ጥቅማጥቅሞች ያቀርባሉ። ሌሎችም አገልግሎቶች ሊያቀርቡና የፋይል አስተዳዳሪም ሊያቀርቡልዎት ይችላሉ።

ከእነዚህ የጤና ዋስትናዎች ሁለቱ፥ United HealthCare (ዩናይትድ ሄልዝኬር) እና Cigna (ሲግና) ከዲስትሪክቱ የሜዲኬድ ኤጀንሲ ጋር ልዩ ስምምነት አላቸው። ይህ ስምምነት በሜዲኬርም በሜዲኬድም ውስጥ ለተመዘገቡ ሰዎች አገልግሎት እንዲያቀርቡ ይፈቅድላቸዋል። እንዴ ሌሎቹ ዋስትናዎች፥ በሜዲኬር fee-for-service በኩል የሚያገኟቸውን ዓይነት ተመሳሳይ ጥቅማጥቅሞች ያቀርባሉ። ሆኖም ተጨማሪ ጥቅማጥቅሞች ያቀርባሉ፥ ሕክምናዎንም ማስተባበር ያግዙዎታል።

የግል የጤና ዋስትና ውስጥ ከተመዘገቡ በሜዲኬር fee-for-service በኩል የሚያገኟቸውን የሕክምና አቅራቢዎች በሙሉ ላያገኙ ይችላሉ። ሆኖም፥ እያንዳንዱ ዋስትና ታካሚዎቹን ለማገልገል የሚያስችል በቂ ዶክተሮችና ሌሎች አገልግሎት አቅራቢዎች ሊኖሩት ይገባል።




በመጨረሻም ከሐኪም የታዘዝዎለትን መድኃኒት (Part D) ጥቅማጥቅሞችን የሚረዳ የተለየ ኩባንያ ሊኖርዎት ይችላል። ወይም ሌሎች የሜዲኬር ጥቅማጥቅሞችዎን የሚያቀርበው ኩባንያ እራሱ ሊሆን ይችላል።

<u>**ሜዲኬድ**</u> ከፌዴራል መንግሥት ጋር የተቀናጀ እያንዳንዱ ስቴት የሚያስተዳድረው መርሃ ግብር ነው። በገቢያቸው፥ በአካል/አእምሮ ጉዳታቸው፥ በዕድሜያቸው ወይም በሌሎች ምክንያቶች ብቁ ለሆኑ ሰዎች የሕክምና ሽፋን ይሰጣል። ልክ እንደ ሜዲኬር፥ መሠረታዊ የሕክምና ጥቅሞችን ይሸፍናል፥ ግን ሜዲኬር የማይሸፍናቸውን ብዙ ነገሮች ይሸፍናል። ለምሳሌ የረጅም ጊዜ እንክብካቤን፥ የጥርስ ሕክምናን፥ የመስማትና የማየት ጥቅማጥቅሞችን ይሸፍናል። በሁለቱም መርሃ ግብሮች ለተመዘገቡ ሰዎች የሜዲኬድ ሽፋን በሜዲኬር ጥቅማጥቅሞች “ዙሪያ ይጠቀለላሉ”። ይህ ማለት ሁለቱም መርሃ ግብሮች የሕክምና ሽፋን የመስጠት ኃላፊነትን ይጋራሉ ማለት ነው።

በዲስትሪክቱ ውስጥ ልክ እንደ ሜዲኬር፥ የሜዲኬድ ሽፋን ሊኖርዎት የሚችልባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ። የግል ሜዲኬድ የጤና ዋስትናዎች በዲስትሪክት ሜዲኬድ ውስጥ ከተመዘገቡት ሰዎች ውስጥ 80 በመቶውን ያህል ይሸፍናል። እነዚህ ዋስትናዎች – ለምሳሌ AmeriHealth Caritas DC (አሜሪሄልዝ ካሪታስ ዲሲ) እና CareFirst DC (ሜድስታር ፋሚሊ ቾይስ) – ሁሉንም የሜዲኬድ አገልግሎቶች ይሸፍናሉ። ሆኖም እነዚህ ዋስትናዎች ሁለቱም ሜዲኬርም ሜዲኬድም ያላቸውን ሰዎች ባብዛኛው አይሸፍኑም።

ሜዲኬር ያላቸው ሰዎች ሜዲኬድ fee-for-service (አንዳንዴ “ቀጥተኛው ሜዲኬድ” ተብሎ የሚጠራው) ውስጥ መመዝገብ ይችላሉ። ብዙ የአካል/የአእምሮ ጉዳት ያላቸው ሰዎች ወይም አዛውንቶች ሜዲኬድን መጣያ መርሃ ግብር ውስጥ ይመዘገባሉ። መጣያዎች ለሚያስፍልጓቸው ሰዎች ተጭማሪ ጥቅማጥቅሞችና አገልግሎቶች ሊያቀርቡ ይችላሉ። በዲስትሪክቱ ውስጥ ሶስት መጣያ መርሃ ግብሮች አሉን፡- EPD፥ IDD፥ እና IFS። የEPD ማስቀሪያ አዛውንቶችን ወይም የአካል ጉዳት ያላቸውን ሰዎች ያገለግላል። የIDD እና የIFS መጣያዎች የአእምሮ ወይም የእድገት ጉዳቶች ላላቸው ሰዎችና ለቤተሰቦቻቸው ድጋፍ ይሰጣሉ።



አንዳንድ ከሜዲኬርም ከሜዲኬድም እገዛ የሚያገኙ ሰዎች ሙሉ የሜዲኬር ሽፋን ያላቸው ቢሆንም የሜዲኬድ ጥቅማጥቅሞች ማግኘት አይችሉም። እነዚህ ሰዎች ብዙውን ጊዜ “QMBs” (Qualified Medicare Beneficiaries (ብቃት ያላቸው የሜዲኬር ተጠቃሚዎች) ተብለው ይገለጻሉ። የሜዲኬድ ጥቅማጥቅም የማግኘት ብቃት ባይኖራቸውም የሜዲኬድ ኤጀንሲ ለሜዲኬር ጥቅማጥቅሞቻቸው ክፍያ እገዛ ያደርጋል።

# በ2022 ዓ.ም. የሜዲኬርና የሜዲኬድ ለውጦች እንደሚኖር ሰምቻለሁ። ምንድነው የሚለወጠው? ምን ማድረግ አለብኝ?

በዲስትሪክቱ ውስጥ የሚኖሩ ከ36000 በላይ የሚሆኑ ሰዎች የተወሰነ ዓይነት የሜዲኬር ሽፋን ሕና የተወሰነ ዓይነት የሜዲኬድ ሽፋን አላቸው። ከአንድ በላይ የሕክምና ዋስትና ሲኖርዎ ግራ የሚያጋባና ውስብስብ ሊሆን ይችላል። የዲስትሪክቱ አስተዳደር ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን አገልግሎት በቀላሉ እንዲያገኙና እንዲጠቀሙ ማድረግ ይፈልጋል። ይህን ለማድረግ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሜዲኬድ ኤጀንሲ የሆነው የDC Department of Health Care Finance (DHCF) (የዲሲ የጤና እንክብካቤ ፋይናንስ መምሪያ) አዳዲስ መርሃ ግብሮች እየጀመረና ነባር መርሃ ግብሮችን እያስፋፋ ነው።

## PACE (ፔስ)

የProgram of All-Inclusive Care for the Elderly (የአረጋዊያን ሁሉን አቀፍ እንክብካቤ መርሃ ግብር) በ2022 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ዲስትሪክቱ ይመጣል። PACE በሌሎች ስቴቶች ውስጥ ለብዙ ዓመታት ሲሠራ የቆየ ሞዴል ነው፥ የዲስትሪክቱም የመጀመሪያ የ PACE መርሃ ግብር ለዎርድ 7 እና 8 አገልግሎት ይሰጣል። PACE በብዙ መልኩ ለየት ያለ ነው። የሜዲኬርና የሜዲኬድ አገልግሎቶችን እንደ "ሁሉን አዘል ሱቅ" ለማቀናጀት ይፈቅዳል። ይህ የሚካሄደው በማህበረሰብ አቀፍ "interdisciplinary care team"ን ("ሁለገብ የእንክብካቤ ቡድን") ወይም IDTን የሚያካትት PACE ማዕከል ውስጥ ነው። IDTው የ PACE ተሳታፊዎች ፍላጎት መሟላቱን ለማረጋገጥ አብረው የሚሠሩ 11 የተለያዩ የPACE መርሃ ግብር የቡድን አባሎች አሉት።

በPACE ውስጥ ከተመዘገቡ፥ አገልግሎት ሠጪዎ ከ PACE ቡድን ጋር አብሮ ላይሠራ ስለሚችል ሌሎች አሁን የሚጠቀሟቸውን አገልግሎቶች ላያገኙ ይችላሉ። ሆኖም የPACE መርሃ ግብር ሁሉንም ሜዲኬርና ሜዲኬድ የሚያቀርቧቸውን አገልግሎቶች በሙሉ ማቅረብ አለበት። በማህበረሰቡ ውስጥ ደህንነትዎንና ጤናዎን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉት አገልግሎቶች በሙሉ በአገልግሎት ዋስትናዎ ውስጥ መካተታቸውን ለማረጋገጥ ከእርስዎና ከቤተሰብዎ ጋር አብረው ይሠራሉ።

የሜዲኬር ጥቅማጥቅሞችዎን ለማግኘት ባሁኑ ጊዜ United ወይም Cigna ውስጥ ተመዝግበው ከሆነ፥ በ2022 ዓ.ም. አገልግሎቶች እንዴት እንደሚቀየሩ ለማወቅ የጤና ዋስትናዎን ወይም የእንክብካቤ ቡድንዎን ያነጋግሩ። በ United ወይም በCigna ውስጥ *ሕንዲሁም* የEPD ማስቀሪያ ውስጥ ተመዝግበው ከሆነ የEPD ማስቀሪያ ፋይል አስተዳዳሪዎንም ያነጋግሩ።

## Dual Choice (ዱዋል ቾይስ)

ዲስትሪክቱ አሁን ያለውን የDual Choice መርሃ ግብር ልዩ የ Medicare Advantage (ሜዲኬር አድቫንቴጅ) የጤና ዋስትናዎች በመጨመር እያስፋፋው ይገኛል። United HealthCare እና Cigna ባሁኑ ወቅት እዚህ መርሃ ግብር ውስጥ ያሉን ዋስትናዎች ናቸው። ባሁኑ ጊዜ በሁለቱም በ Medicare Advantageም (ሜዲኬር አድቫንቴጅ) በሜዲኬድ ውስጥም የተመዘገቡ ሰዎች የሜዲኬድ ጥቅማጥቅሞቻቸውን በfee-for-service ሜዲኬድ በኩል የሚያገኙ ሲሆን የሜዲኬር ጥቅማጥቅሞቻቸውን በጤና ዋስትናው በኩል ያገኛሉ። በ2022 ዓ.ም. የጤና ዋስትናዎቹ የሜዲኬድ ጥቅማጥቅሞች የሚያቀርቡ ሲሆን፥ ሁለቱንም አገልግሎቶች እንደ "ሁሉን አዘል ሱቅ" ይቀላቅላቸዋል። ይህም የጤና ዋስትናዎቹ በሁለቱም መርሃ ግብሮች በኩል ይበልጥ የተቀናጁ ጥቅማጥቅሞች እንዲያቀርቡ ይረዳቸዋል።

በDual Choice ውስጥ ከተመዘገቡ፥ አገልግሎት ሠጪዎ ከጤና ዋስትናው ጋር አብሮ ላይሠራ ስለሚችል ሌሎች አሁን የሚጠቀሟቸውን አገልግሎቶች ላያገኙ ይችላሉ። የሜዲኬር ጥቅማጥቅሞችዎን ለማግኘት አሁን በDual Choice ተመዝግበው ከሆነ *የሜዲኬድ ጥቅማጥቅሞችዎ* ላይ ለውጥ ሊያዩ ይችላሉ (ለምሳሌ የቤት ውስጥ ሕክምና ወይም የ EPD ማስቀሪያ ጥቅማጥቅሞች)። ሆኖም ሁሉንም የሜዲኬርና የሜዲኬድ አገልግሎቶች የማግኘት መብት አሁንም ይኖርዎታል። በማህበረሰቡ ውስጥ ደህንነትዎንና ጤናዎን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉት አገልግሎቶች በሙሉ እና የመረጡት አገልግሎት ሰጪ ዋስትናዎ ውስጥ መካተታቸውን ለማረጋገጥ ከእርስዎና ከቤተሰብዎ ጋር አብረው ይሠራሉ።

በ2022 ዓ.ም. ለመመዝገብ እንዲያስቡበት ስለ Dual Choice ወይም PACE የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ የሕክምና አቅራቢዎችዎን ወይም የ DC State Health Insurance Program (የዲሲ ስቴት የጤና ዋስትና መርሃ ግብር) (SHIP፡- 202-727-8370)ን ያነጋግሩ።